# ሻለቃ ጌታቸው የሮም

(፲፱፻፴፪ ኢትዮጵያ ፡ ፪ ሺህ ፪ ዓ/ም አሜሪካ)



## Major Getachew Yerom

(1940 Ethiopia – 2010 USA)

# የሻለቃ ጌታቸው የሮም
# <u>አጭር የሕይዎት ታሪክ</u>

ሻለቃ ጌታቸው የሮም ከአባታቸው ከቀኛዝማች የሮም ተሰማ እና ከእናታቸው ከወይዘሮ ሰገዱ ባብል በ1932 ዓ/ም በጎጃም ክፍለ-አገር በቡሬ ዳሞት አውራጃ ልዩ ስሙ ጣልያ ልጅ አምበራ ክብበብ-ገብርኤል በሚባለው ሥፍራ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምሕርት ሲደርስ በአካባቢው በሚገኙት የተለያዩ መንፈሣዊ ትምሕርት ቤቶች ገብተው ባሕላዊ ትምሕርቶችን ቀስመዋል። በመቀጠልም በመጀመሪያ ቡሬ ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም ትምሕርት ቤትና ከዚያም ደጀን በሚገኘው ትምሕርት ቤት ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚሰጠውን ትምሕርት አጠናቀዋል።

ሻለቃ ጌታቸው ገና ከልጅነት ጀምሮ ለላቀ ትምሕርትና እውቀት በነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት ተነሳስተው ከጎጃም ወደ አዲስ አበባ በራሣቸው ፈቃድ በመሄድ የፖሊስ ሠራዊትን ተቀላቀሉ። የሰላ አእምሮአቸውና ቅልጥፍናቸው በፖሊስ ሠራዊት ውስጥ የሚሰጡትን የመገናኛና ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን ለመውሰድና በሚያኮራ ውጤት ለማጠናቀቅ አስችሏቸዋል። በሰለጠኑባቸው ሙያዎችም በመደበኛ ፖሊስና በፈጥኖ ደራሽ ምድቦች ከአዲስ አበባ ጀምሮ በልዩ ልዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከፍተኛ አገልግሎቶችን በመስጠት በትጋታቸውና ባስመዘገቧቸው ውጤቶች ለመኮንንነት ማዕረግ በቅተዋል። ሻለቃ ጌታቸው ተዘዋውረው አገልግሎት ከፈፀሙባቸው የኃላፊነት ቦታዎች አንዱ የደብረ-ዘይት የፖሊስ አዛዥ በመሆን ነበር።

ንጉሠ-ነገሥቱ ሣምንታዊ የእረፍት ጉብኝት በሚያደርጉባት፣ የአገሪቱ የአየር ወለድና የአየር ኃይል ጠቅላይ ሠፈሮች ማዕከል በሆነችው በዚች ፀጥታ የመጀመሪያ ደረጃ ህሳቦት በሆነባት ቁልፍ ከተማ በፖሊስ አዛዥነት የሚመደብ መኮንን ምን ያኽል ኃላፊነት እንደሚጠበቅበት፣ ታማኝነትና ሁሉን-አቀፍ ብቃትና ችሎታን እንደሚጠይቅ የታወቀ ሲሆን፣ ሻለቃ ጌታቸው የሮም የነበራቸው ንቁነት፣ የሥራ ብቃትና ችሎታ ለዚች ከተማ የፖሊስ አዛዥ እንዲሆኑና ኃላፊነታቸውንም ጠፈፍ ባለ ሁኔታ እንዲወጡና ለበለጠ እድገትና ማዕረግ እንዲበቁ አስችሏቸዋል።

ከስድሣ-ስድስቱ ለውጥ በኋላም በለውጥ ኃዋርያነት ያገለገሉ ሲሆን፣ የነበልባል ጦር ሲቋቋም በወታደራዊ ንቃታቸውና የአመራር ችሎታቸው ተመርጠው ከተመደቡት መኮንኖች አንዱ ሻለቃ ጌታቸው የሮም ነበሩ። ነበልባል ጦር ውስጥ ከአሠልጣኝነት እስከ ሻለቃ ጦር መሪ በመሆን አገልግለዋል። ደርግ የተያያዘው ኢ-ፍትኃዊ አሠራርና የተከተለው አጥፊ መንገድ ለአገራችን የማይበጅ መሆኑን በመረዳትና በውስጥ ሆኖ ለውጥ ለማምጣት እንደማይቻል የተገነዘቡት ሻለቃ ጌታቸው በመጀመሪያ ወደ ሱዳን በመውጣትና ተመልሰው ወደሚወዷት አገራቸው በመግባት ለቆሙበት ሕዝባዊ ዓላማ ሕይዎታቸውን ለመስጠት በመወሰን በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት የሚደረገውን የትጥቅ ትግል ተቀላቀሉ።

ሁኔታዎች ዳግም ወደ ሱዳን እንዲወጡ ቢያስገድዷቸውም፣ ሻለቃ ጌታቸው ከመሰል ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ልዩ ልዩ አገር-አቀፍ ድርጅቶች በማቋቋምና የአመራር አባል በመሆን ታግለዋል። በዚሁም መሠረት በመጀመሪያ በሱዳን ከዚያም በአሜሪካ በስደት በቆዩባቸው ጊዜዎች ሁሉ በኢትዮጵያ አገር-ወዳዶች ድርጅት፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ በክተት-ኢትዮጵያ፣ በነፃ ወታደሮች ንቅናቄ፣ ወዘተ ንቁ ተሣትፎ በማድረግ በድርጅቶቹ የአመራር አባል ሆነው ታግለዋል። ሻለቃ ጌታቸው ይኸን ለአገርና ለሕዝብ ያላቸውን ከፍተኛ ፍቅር እስከ ዕለተ-እረፍታቸው በታማኝነት ተወጥተዋል።

በተጨማሪም፣ ሻለቃ ጌታቸው ታሪክንና የቅርብና የሩቅ ተመክሮን ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ ባላቸው ዕት ፍላጎት፤ 1ኛ. የኢትዮጵያን ሕዝብ የለውጥ እንቅስቃሴ በተመለከተ "የለውጥ ረመጥ የታሪክ ማስታወሻ"፣

2ኛ. ለአሥራ-ሰባት ዓመታት በወታደራዊ አገዛዝ የተካሄደውንና የደረሰውን አጠቃሎ የሚገልፅ "ፍረጅ ኢትዮጵያ"፣ እና

3ኛ. በመጨረሻም የአገራችንን አርበኞችና ባለውለታዎች በዝርዝርና በምስል (ፎቶግራፍ) በተደገፈ አብራርቶ የሚያስረዳ “ስም ከመቃብር በላይ” የተሰኙ መፃሕፍትን ያበረከቱ ደራሲ ሲሆኑ፤ ሌላም አራተኛ ታሪካዊ መፀሐፍ ለማዘጋጀት ደፋ-ቀና ሲሉ እንደነበር ታውቋል።

ሻለቃ ጌታቸው የሮም በሥራ ዘመን ባልደረቦቻቸው፣ የበታቾቻቸውና አለቆቻቸው፣ በትግል ጓዶቻቸውና በዘመድ-አዝማዳቸው ሁሉ የተከበሩና የተወደዱ፣ ሰው-አክባሪ፣ ቁጡብ፣ ባህላቸውንና ሐይማኖታቸውን አክባሪ፣ ቅን፣ ቸር፣ ርኅሩኅና ታታሪ፣ ቆፍጣና፣ ቆራጥ አገር-ወዳድና መንፈሰ-ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ነበሩ።

ሻለቃ ጌታቸው ዕድሜአቸውን ሙሉ አገራቸውን በመንግሥት ሥራ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ያገለገሉ፣ ከልባቸው ለሚወዷት አገራቸውና ለሚያፈቅሩት ሕዝባቸው የፍትኅና የዴሞክራሲ ዓላማ በተሠማሩበት ትግል እና በስደት ያሳለፉ ቢሆንም የልጆች አባትና የልጅ ልጆችንም ለማየት ዕድል ገጥሟቸዋል። በመሆኑም፣

1ኛ ሠላማዊት ጌታቸውን

2ኛ. ዶክተር ኢሌኒ ጌታቸውን

3ኛ. ዮሐንስ ጌታቸውን

4ኛ. ሣሙኤል ጌታቸውን

5ኛ. አሌክሳንደር አሰፋ ጌታቸውን አፍርተዋል።

ሻለቃ ጌታቸው የሮም በአደረባቸው ሕመም ምክንያት ለአጭር ጊዜ የሕክምና እርዳታ እየተደረገላቸው በነበሩበት በሆሊ ክሮስ ሆስፒታል (ሜሪላንድ ) ዓርብ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፪ ሺህ ፪ ዓ/ም (July 23, 2010) ምሽቱ ላይ በተወለዱ በሰባ ዓመታቸው ከሚወዷቸና ከሚያፈቅሯቸው ልጆቻቸው፣ እህቶቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው፣ ወዳጆቻቸው ተለይተውና ዕድሜአቸውን ሁሉ በታማኝነት ያገለገሏትንና የታገሉላትን ውድ አገራቸውን እንደናፈቁ ተመልሰው ሳያዩአት ከዚኽ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ቅኑውና አርበኛው ሻለቃ ጌታቸው እረፍታቸው ከአገራቸው ውጭ ቢሆንም ታመው ሐኪም ቤት ከገቡበት ቀን ጀምሮ እስከ ዕለተ-እረፍታቸው ድረስ የልጆቻቸው፣ የእህታቸው፣ የእህቶቻቸው ልጆች፣ የቅርብ ዘመድ አዝማድና የወዳጆቻቸው ሙሉ ፍቅርና እንክብካቤ አልተለያቸውም።

፲፱፻፴፪ – ፪ ሺህ ፪ ዓ/ም (1940 – 2010)

---------- // ------------

“ትንሣዔና ሕይዎት እኔ ነኝ፣ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳን ሕያው ይሆናል። ሕያው የሆነም የሚያምንብኝ ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም።” ዮሐንስ ፲፩፤ ፳፭ -፳፮

የበረሃው ጀግና የኢትዮጵያ ልጅ
እንዴት ለበሽታ ትሰጣለህ እጅ፡
የሶማሌን ታሪክ የኦጋዴን ትግል
አሸንፈህ መጥተህ ደከመኝ ሳትል፡
ጠይቀን ነበረ እንድትነግረን
ስለ ጠረፍ ውጊያ ያወራኸውን፡
ማወቅ ያለበትን ያሁኑ ትውልድ
መማር ስላለበት አገርን መውደድ፡
ተስማምተህ ነበረ ልትነግረን ታሪክ
ገና ሳትጀምር እጅህን ታሰርክ፡
የፖሊስ ሠራዊት የፈጥኖ ደራሽ

የአገሩን ጠላት መክቶ መላሽ
ከልጅ ከእህቶቹ አየነው ሲሸሽ፡
ሻለቃ ጌታቸው ቁም-ነገረኛው
ለአደራ እንዳይበቃ ሞት አታለለው፡
ፈጥኖ ደራሽ ነበር ለቤተሰብ ሁሉ
አስደነቀን በጣም ለሞት መታለሉ፡
ደኅና ሁን ጌታቸው የኢትዮጵያው ጀግና
ታሪክህ አይሞትም ይሆናል ገናና
የኢትዮጵያ አርበኛ ታብባለህ ገና፡

በል ደኅና ሁን ጌታቸው!

(ከባለቤቱ ወይዘሮ ርብቃ ወልደ ማርያም)

------------- // --------------

## ጌትሽ

ምነው ከቤ? ምነው ጌትሽ መቻኮልህ
ዓለማየሁ ነው ወይስ ፈለቀ የናፈቁህ?
ከልጆችህ፣ ከእህት ወንድሞችህ፣
ከዘመድ አዝማድ ሁሉ እነሱ በለጡብህ?
እንደዋዛ ወጥተህ ሳትመለስ መቅረትህ?
አዬ ጌትሽ 'ፍረጅ ኢትዮጵያ' አልክ?
መልሱ ግን ዘገየብህ ብዙ ጠበክ።
ብይኑን እዚህ እንደማታገኝ አውቀህ፣
ምናልባት በዚያኛው ዓለም ቢገኝ ብለህ
ይሆን እንዴ መጣደፍህ፣ መቻኮልህ?
አዬ አንች ጉደኛዋ አገራችን፣
የሁላችን ቤት አለኝታችን፣
የምንወድሽ ኢትዮጵያችን።
ምነው ዳተኛ ሆንሽበት በፍርድሽ
ሆነሽ ሳለ የተቀደስሽ የተባረክሽ፣
እኮ ለምን የናፈቁሽን ማራቅሽ
የሚጠሉሽን ማክበርሽ?
ይሁንናም ጠልቶ ከመከበር
ቀለማምዶ መስሎ ከመኖር።
እንደወደዱሽ ማለፉን፣
እንደናፈቁሽ መቅረትን።
እምነት እስከ ሞት ብለው፣
አሁም እንደወትሮው እንደሁሌው።
ያው አልጠፉም የነደዱ በፍቅርሽ፣
የማይተኙ ስለአንድነትሽ ስለሕዝብሽ።
የስደት ሞትን የመረጡ
እንደወደዱሽ ለመለየት የቆረጡ።
ለምን ይሆን የትግል ጓደኛ ሲለየን፣
እርር ድብን፣ ምርር ኩምትር የሚያደርገን።
ከላይ ሣይሆን ውስጥ ውስጡን የሚበላን፡
የማይረሣ ሰቀቀን የሚሆንብን?

እዎን፣ አሁን አሁንስ ገባኝ
እጅግ በጣም ተረዳኝ
ለካስ ኖሯል ልማዳችን
የጠነከረ እምነታችን::
አንተ ብላ በኔ ፈንታ፣
እኔ ልሙት ባንተ ቦታ::
ብሎ እራሱን የሚያሳልፍ፣
ለውለታ ሣይሆን ወይም ለትርፍ::
ለደግ ደጉ፣ ለበጎው ጓዱን የሚያስቀድም፣
ዓይኑን ሳያሽ፣ ሳያቅማማ ሳያዳግም፣
እራሱን ቀድሞ አቅራቢ ለችግር ይሁን ለሞትም::
ከጭቆና ፍትኅን ከውርደት ነፃነትን የመረጠ
አጥንት ያልቆጠረ ጎሣ ያላበላለጠ
በሕይዎቱ ሕይዎትን ለመታደግ የቆረጠ::
ከፉፉይ አረመኔ እንጂ ባዕድ የለው
ለሱ ሁሉም ያው አንድ ወጥ ወገኑ ነው::
የሚታየው፣ ያመነበት፣ በተግባርም የገለፀው
ጌታቸውም የታገለው ለዚሁ ነው::
በል ጌትሽ መንገድህ መልስ የሌለው አንድ-ወጥ ነው ፣
ለጊዜው ነው የተለየኸ እኛ እስክንመጣ ወዳንተው::

(ከትግል ጉዱ፡ አያል-ሰው ደሴ)